# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 38 ኛ ሳምንት

## ነቢዩ ኤልያስ በቁራዎች ተመገበ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ትዕዛዙን ለሚፈጽሙ የሚያደርገውን እንክብካቤ መማር፡፡

**ምንባብ**

- 1ኛ ነገ. 17፣ 1-7

**መግቢያ**

- ዛሬ ኤልያስ ስለሚባል ነቢይና የእግዚአብሔር ሰው ሲሆን የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ የሚያደርስ እና ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ የሚያስተምር ነው፡፡

**ትምህርቱ**

- አክዓብ የተባለ የእስራኤል ንጉሥ ነበር፡፡ጣዖት አምላኪም ነበር፡፡ጣዖት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሰዎች የሚሰውላቸውና የሚያመልኳቸው በእጃቸው የሚሠሩት ሐውልት ነው _ ጣዖት፡፡
- ይህም ***"የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡፡ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም፣..."*** የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ መቃረን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኤልያስ ዝናብ እንደማይኖር ለአክአብ ነገረው ውጤቱም ረሀብ ሆነ፡፡
- ኤልያስ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለጠበቀ፣ ወደ አንዲት ትንሽ ወንዝ እንዲሄድና ቁራዎች እንዲመግቡት እግዚእብሔር አዘዘለት፡፡
- ቁራ የአዕዋፍ ዝርያ ሆኖ ንስር የሚመስል ትልቅ ርግብ ነው፡፡ ኤልያስም እግዚአብሔር ወዳዘዘው ሥፍራ ሄደ፡፡ ቁራዎቹም በየዕለቱ ዳቦና ሥጋ ያመጡለታል፣ ከትንሿ ወንዝ ምንጭም ይጠጣ ነበር፡፡

**ማጠቃለያ**

- ሁሌም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ አለብን፡፡ ይሄንን ስናደርግም እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ ይጠብቀናል፡፡
- በአክዓብና በሕዝቡ ኃጢአት ዝናብና ምግብ አልነበረም ፡፡
- እግዚአብሔር ግን ሥጋና ዳቦ ኤልያስን እንዲመግቡ ቁራዎችን ልኮለታል እግዚአብሔር እኛንም ይጠብቀናል፡፡

**መልመጃ**

1 ጣዖታት ምንድን ናቸው?

2. እግዚአብሔር ኤልያስ የት እንዲሄድ አዘዘው ?

3. እግዚአብሔር እንዴት ጠበቀው?

**መዝሙር**

| | |
|---|---|
| ኢትግድፈነ(2) ወኢትመንነነ (2) | አትተወን(2)አትናቀንም |
| አምላከ ሰላም ተረድኣነ(4) | የሰላም አምላክ ሆይ እርዳን፡፡ |

# A Raven



ይቆየን፡፡